የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፸፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year, No.75
ADDIS ABABA, 18th ,May 2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግስት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.................................................................................፱ሺ፷ ፮

## CONTENTS

Proclamation No.951/2016

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation.....page 9066

አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፩/፪ሺ፰

**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት ሚያዚያ ፬ ቀን ፳ሺ፯ ዓ.ም በአቡ ዳቢ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው

**PROCLAMATION No. 951/2016**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMNT OF THE UNITED ARAB EMIRATES FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME**

**WHEREAS,** an Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income has been signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates on the 12th day of April 2015, in Abu Dhabi;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said convention at its session held on the 19th day of April 2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ታውጇል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግስት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፩፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ መንግስት መካከል ሚያዚያ ፬ ቀን ፳ሺ፯ ዓ.ም በአቡ ዳቢ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No. 951/2016".

**2. <u>Ratification of the Convention</u>**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Government of the the United Arab Emirates for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on the 12th day of April 2015 is hereby ratified

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned government organs.

**4. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 18th day of May, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት